# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

ቁጥር 25 ቀን 17/8/67

## የኢንዶቻይና ተራማጅ ሕዝቦች ኢምፔሪያሊዝምን አንበረከኩት

በካምቦዲያ ነፃአውጭ ግንባር የሚመራው ሰፊው ተራማጅ የካምቦዲያ ሕዝብ በሚያዝያ 9 ቀን ዋናውን ከተማ ኖምፔንን አስለቀቀ፤ ካምቦዲያ አሁን ሙሉ በሙሉ ነፃ ወጥታለች፡፡ የመጨረሻዎቹ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አሻንጉሊቶች የእጅ መስጠት ድርድራቸውን አርበኞቹ ውድቅ እንደአደረጉት ህይወታቸውን ለማዳን ብቻ ሹልክ ሹልክ እያሉ ከአገር ወጥተዋል፡፡በቪየትናም ደቡባዊ ክፍል/ደቡብ ቪየትናም/ የነፃ አውጭ ሃይሎች ከምን ጊዜውም ይበልጥ ሃይላቸውን በማጠንከር ከሰላሳ አመታት በላይ የተዋጉለትና ደማቸውን ያፈሰሱለትን ነፃነት በሙሉ ወደማግኘት የተቃረቡ መሆናቸውን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እንኳን ለማመን ተገድዶአል፡፡ ነፃአውጭ አርበኞቹ በቀርቡ ሳይጎንን በመያዝ መላውን የቪየትናም አገር ነፃ እንደሚያወጡ ዛሬ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡በካምቦዲያ መሪ አሻንጉሊት የነበረው ሎንኖል በነፃ አውጭዎቹ አርበኞች ተወጥሮ በመያዙና ቀኖቹ መቃረባቸውን በማያጠራጥር አኳኋን ስለተረዳ አሞኛል፡ኢንዶኔዥያ 'እረፍት' እወስዳለሁ፡'ለህክምና' ወደአሜሪካ እሄዳለሁ፡ወዘተ. ብሎ በመቀባጠር ከካምቦዲያ ከፈረጠጠ ሳምንታት ሆነዋል፡፡በደቡብ ቪየትናማውያን ላይ ተጭኖ የነበረውም ቲዩ የሎንኖል ጽዋ እንደማይቀርለት በመገንዘብ ከስልጣን ወርዶአል፡፡

የእነዚህ አሻንጉሊቶች ፈጣሪና ጌታ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፡የደረሰበትን ታላቅ ውርደትና መሸነፍ ለመሸፈን ልኡል ሲሃኑክን ይምጡና የመንግስቱን ስልጣን ይረከቡ፤ ካምቦዲያኖች ጉዳያችሁን 'ራሳችሁ' ፈጽሙ፤ በመግባባትና በሰላም 'አንድነታችሁንና ነፃነታችሁን' ጠብቁ ወዘተ.፡ በማለትና በቪየትናምም የእርቅ ድርድር እናድርግ እያለ ለማወናበድ ከሞከረ በሁዋላ፡ነገሩ 'ጅብ ከማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ' እንደሚባለው ሆነና ጓዙን ጠቅልሎ መውጣት ጀመረ፡፡ የካምቦዲያና የቪየትናም ተራማጅ አርበኞችና ሰፊው ሕዝብ አፈር አስግጠውና በጦር ሜዳ ላይ አንበርክከው፡ለዘለአለም የማይፋቅ ውርደትና ሃፍረት አትመውበት ድል በመምታት ቅስሙን ሰብረው ከአገራቸው አስወጡት፡፡

ባሁኑ ጊዜ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ቀንደኛ የሆነው አሜሪካ በኢንዶቻይና ሰፊ ሕዝቦች 'የማርያም ጠላት' ተብሎ ራሱን እንደአባብ በመወገርና በመቀጥቀጥ ላይ ነው፡፡ገና ታዳጊና ደካማ ሕዝቦች በአለም ተወዳዳሪ የሌለውን የኢምፔሪያሊስት ሃይል በጦር ሜዳ በማንበርከክና ድል በመምታት ላይ ናቸው፡፡ለመሆኑ የአለም ሕዝቦችን ነፃነት ለመግፈፍና ለመበዝበዝ ቆርጦ የተነሳውንና በዘመናዊ መሳሪያ ከራስ ጠጉሩ እስከእግር ጥፍሩ የታጠቀውን የኢምፔሪያሊስት ሃይል ማሸነፍ የቻሉት እንዴት ነው?

ይህ ድል የተገኘው ቁራጥነት በተመላበት የሕዝብ ትግል እንጂ በመሳሪያ አይነትና ብዛት አይደለም፡፡በዚህም የቪየትናምና የካምቦዲያ ሕዝቦች ለመላው አለም ትልቅ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡ በጦርነት ለማሸነፍ ከዘመናዊ መሳሪያ ጋጋታ ይልቅ ትክክለኛ አላማን ይዞ የሚዋጋ ሕዝብ ይበልጥ ቀዋሚነት እንዳለው አሳይተዋል፡፡ሕዝባዊ ጦርነት በማድረግ አንድ ትንሽ አገር ትልቁን የኢምፔሪያሊስት ሃይል ማሸነፍ እንደምትችል በተግባር አስመስክረዋል፡፡ የቪየትናምና የካምቦዲያ ሕዝቦች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምንና ቡችሎቹን በጦር ሜዳ ድል መምታት የቻሉት አላማቸው ትክክለኛ አላማ ስለሆነ፡የሃገር ፍቅርንና ሶሻሊዝምን በሚገባ ስላዋሃዱ፡የሕዝባዊ ጦርነትን ህጎች በሚገባ በስራ ላይ ስላዋሉና ከብረት የጠነከረ ዲሲፕሊን ስላላቸው ነው፡፡

